# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)
## Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

ኅዳር 27 ቀን 2006 ዓም
December 6, 2013

## ደህና ሁን ኔልሰን ማዲቦ ማንዴላ ! / እንሰናበትህ ፥ ኔልሰን ማዴላ !

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ ) ኔልሰን ማንዴላ ከዚህ ዓለም በመለየቱ ምክንያት የተሰማውን መሪር ሀዘን ለመላው ቤተሰቦቹና ለደቡብ አፍሪካ ሕዝብ ያስተላልፋል።

ለእኛ፥ ኔልሰን ማንዴላ፥ የመንፈስ ጥንካሬ፥ የአይበገሬነት፥ የዓላማ ፅናት፥ የዕምነት ታማኝነት፥ የይቅር ባይነትና የሰላም ዓርአያ ነው። የዴሞክራሲ ራዕይም ተምሰሌት ነው። እነኝህን ክቡር ዓላማዎች አንግቦ፥ ፀንቶ እስከ ፍፃሜ ሕይወቱ በመታገሉም፥ እናከብረዋለን።ጠላቶችን ይቅር በማለት የታላቅነት መግለጫ በማሳየቱም፥ ዓርዓያነቱ ዘለዓለማዊ ነው። ከድል በኋላ ከባላንጣዎቹ ጋር ተስማምቶና ተቻችሎ፥ ያለፈውን ግፍና በደል ወደ ጎን በመተው ለአገር ሰላምና ለሕዝብ ብልፅግና ከማሰብስ የበለጠ ምን የተሻለ ነገር ይኖራል ? ይህን መሠረታዊ ጉዳይ በተግባር መግለፁን የተመለከቱ አምባገነኖች፥ ትምህርት ሊቀስሙበት ይገባቸዋል። መማር ከፈለጉ !

ኔልሰን ማንዴላ፥ ወገኖቹን ከባርነት ቀንበር ነፃ ለማውጣት ባደረገው ትግል፥ ለሃያ ሰባት ዓመታት በአሰቃቂው እስር ቤት ያሰለፈና ታግሎ ያታገለ ዕውነተኛ ጀግና የሕዝብ ልጅ ነው። ሰብዓዊ ፍጡር ሊሸከመው የማይቻለው ግፍና በደል ቢፈፀምበትም፥ የአፓርታይድን ዘረኛ ሥርዓት ከመታገል ግንባሩን አላጠፈም ። ለግፈኞቹም እጁን አልሰጠም። ድፍረትንና ጥንካሬን አጣምሮ በመያዝ የተሰውቱን የአፓርታይድ ተቃወሚ ታጋዮች በግንባር ቀደም ሲሰዉ ተመልከቷል ። ከነኝህ ሰማዕታት መካከል የእምኮንቶ ዊሲዝዌአባላት፥የፓን አፍሪካ ኮንግሬስ አባላት፥ እንደ ስቲቭ ቢኮ እና ሌሎቹ ብዙሃን ወጣቶች ለታሪክ የሚጠቀሱ ናቸው። ምዕራባውያን ፥ አፓርታይድን ለመደገፍ ሲሉ ፥ ማንዴላን አሸባሪ ነው ብለውት ነበር። የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ አባላትና መሪዎች ፥ በኋላ ላይ ኢሕአፓ የሆነውም ኃይል ጭምር ፥ የአፓርታይድን አገዛዝ ተቃውመዋል ። እንዲሁም የእያን ስሚዝን የሮዲሽያን የጭንጋፍ ነፃነት አዋጅም በግንባር ቀድም ተቃውሟል። የኢሕአፓና የሌሎች አፍሪካውያን የነፃነት እንቅስቃሴዎች ኦፊሸላዊ ግንኙነት የተመሠረተው፥ በአልጀሪያ ዋና ከተማ አልጀርስ ውስጥ በ70 ዎቹ ዓመት ምህረት እንደነበር የኢሕአፓ ታሪካዊ ሰነድ መዝግቦታል ። በርዕዮተ-ዓለምና በወዳጅ ሃይል አሰላለፍ ምክንያት ኢሕአፓና የአፍሪካ ናሽናል ኮንግሬስ፥ልዩነት በነበራቸው ወቅት እንኳ ቢሆን ፥ ኢሕአፓ ፥ የደቡብ አፍሪካን ፀረ- አፓርታይድ ትግል ከመደገፍ ቸል ያለበት ወቅት አልነበረም ።

በትግሉ ዘመን ሁሉ፥ ማንዴላ ግዙፍ አፍሪካዊ ሰብዕና ነበረው። የሀገሩ ፕሬዝደንት ከሆነ በኋላም ቢሆን፥ ትህትና የተላበሰውን ሰብዕና እንደጠበቀ፥ በመርኅ ላይ የተመሰረተ ተግባራትን አከናውኗል። ከዓለም አቀፍ መርኅ አኳያ በመነሳትም ፥ ኢራቅ በውጭ ኃይሎች መወረሯን ተቃውሟል ። የኒዠር ዴልታ ጭፍጨፋንም አውግዟል። ለፍትህ-ርትዕ ለዴሞክራሲና ሰብዓዊ መብቶች ተከራክሯል ።

ኔልሰን ማንዴላ፥ በ1912 ዓም የተመሰረተውን የአፍርካ ናሽናል ( ብሄራዊ) ኮንግሬስን በአርባዎቹ ዓመተ-ምህረቶች ተቀላቅሎ ትግሉን ቀጠለ። የ1956 ዓ.ም. የሻርፔቭልን ዕልቂት ሁላችንም

EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel 202-291-4217 fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com
website: WWW.EPRP.COM

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France

እናስታውሰዋለን ። ይህ ዕልቂት፥ የሶዌቶን መነሳሳት አስከተለ ።ከአያሌ ዘመን ቆራጥ ትግል በኋላ ማንዴላ ከዕስር ተፈትቶ፥ በ1994 ዓ.ም. የደቡብ አፍሪካ ፕሬዝደንት ሆነ ። የነፃነት ትግል የረጅም ዓመታት ተጋድሎና መሥዋዕት እንደሚጠይቅ እንገነዘባልን ። የእኛው የራሳችን ትግልም ቢሆን በዚህ ቅኝት ውስጥ ስለሚካሄድ ፥የኢትዮጵያ ሕዝብ በመጨረሻ ድልን እንደሚጎናፀፍ በጭራሽ አንጠራጠርም ።

የዛሬይቱ ደቡብ አፍሪካ የተለያዩ ችግሮች እንዳሏት እንረዳለን።የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ኑሮ ምስቅልቅሎች እንደተከሰቱባትም እንገነዘባለን ። የሥራ ዕጦቱ፥ የኖሮው ውድነቱና ያልተነመጣጠነ የሀብት ደረጃ እንዳጋጠማት ለማንም ተመልካች ግልፅ ነው ። በደቡብ አፍሪካ የተጠጉ ሌሎች አፍሪካውያን ፥ ኢትዮጵያውያኑም ጭምር፥ የሚደርስባቸውን እንግልትና ያልተረጋጋ ሁኔታ ሳይቀር የምንከታተለው ነው ። ይህ ሀቅ እንዳለ ሆኖ፥ ኔልሰን ማንዴላ አውርሷት በሄደው መልካም ቅርፅ እየተመራች፥ ወደ ዕድገት ጎዳና እንድትቀጥል፥ለደቡብ አፍሪካ መልካሙን ሁሉ እንመኝላታለን ።

ዛሬም ሆነ ወደፊት፥ የማንዴላ የትግል ታሪክ፥ ተግባርና ስብዕና፥ ለአፍሪካ ክፍለ-ዓለም መልካም አርዓያ ሆኑ እንደሚቀጥል፥ለሰብዓዊ ፍጠር መልካሙን የሚመኙ የዓለም ሕዝቦች ሁሉ ተስፋ ያደርጋሉ ።

ኢሕአፓ፥ ለአለፉት አርባ አንድ ዓመታት፥ ለኢትዮጵያ ክብርና ልዕልና ፤ ለዜጎቿ ነፃነትና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በመታገል ላይ ይገኛል ። በሽ የሚቆጠሩ ዜጎቻችን ፥ በቀይ ሽብር ዘመቻ በግፍ ተጨፍጭፈዋል ።በርካታ የሀገሪቱ ታዳጊ ወጣቶች በጭካኔ ድርጊት አካላቸው ተቆራርጦ የአሞራና የአውሬ እራት በመሆን፥የማይቀረውን የጀግና ሞት ተቀብለው በክብር አልፈዋል ። ሌሎቹም አካለ- ስንኩላን ሆነው ቀርተዋል። መዳረሻቸው ያልታወቀውን አሃዝ፥ቤቱ ይቁጠረው ከማለት በቀር፥በአሁን ወቅት ሌላ መናገር አልተቻለም ።

በዘር ላይ የተመሰረተ ጎሰኛ አገዛዘን ከአፓርታይድ ባህረ- መዝገብ የቀዳውና ፀረ-ኢትዮጵያን ፓሊሲውንም ከሙሶሊኒ የቅኝ-አገዛዝ ሰነድ የገለበጠውን ጎሰኛና ዘረኛ ሥርዓት ከምድረ-ኢትዮጵያ እስከተወገደ ድረስ፥ ኢሕአፓ፥ ልክ እንደ ኔልሰን ማንዴላ፥ወያኔን፥ ከነሥርዓቱ ይታገለዋል ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ፥ ትላንት ፥ ኔልሰን ማንዴላ፥ ፀረ አፓርታይድ ትግሉን ሲያካሂድ በጀርባው ሆኖ እንደ ተባበረው ሁሉ፥ዛሬም በመሞቱ ምክንያት ሀዘን ለደረሰበት የደቡብ አፍሪካ ሕዝብ የሀዘኑ ተካፋይ ይሆናል! በአምባገነኖች የምትሰቃየው አፍሪካም ማዴላን የመሰለ ቆራጥ የነፃነት አባት በመፍጠሯ ዕድለኛ ነች !

<u>አንተ ማንዴላ !</u> የሰላም አባት ነበርክና የሰላሙን ዕረፍት አግኝ !
ኢሕአፓም በክብር ይሰናበተሃል ! <u>ደህና ሁን ማንዴላ !</u>

ኢሕአፓ

EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel 202-291-4217 fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com
website: WWW.EPRP.COM

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France